# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ ደን ልማት

## ከ2013 -2015 በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት

መጋቢት 2015

አዲስ አበባ

# ማውጫ

1. ድርሞ/Executive Summary/ ........ 2
2. መግቢያ ........ 6
3. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ ከ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የፊዚካል ስራ አፈፃፀም ትንተና ........ 7
4. የለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ........ 24
5. የኦዲት ግኝት ምልከታ ........ 24
6. የተቋሙ የፋይናንስ/ በጀት አፈፃፀም ........ 26
7. የክትትል እና ግምገማ አፈፃፀም ........ 26
8. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጣሙ ችግሮችና የተወሰዱ/ሊወሰድ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ........ 27
9. ማጠቃለያ ........ 28
10. ዕዝል ........ 29

## 1. ድርሞ/Executive Summary/

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችና ግልጋሎቶች አሉት፡፡ ይህንን ግልጋሎት ከማሳደግ አንፃር ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የሚጠበቁ ውጤቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም እንዲያስችል በየበጀት ዓመቱ ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም በማዕከላትና በዋናው መስሪያ ቤት በሚገኙ አመራሮችና በክልል ባለድርሻ አካላት እንዲገመገም በማድረግና አስፈላጊ ግብዓቶች በመውሰድ በየዓመቱ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ግብዓቱ እንዲካተት በማድረግ የተዘጋጀውን ዕቅድ በማኔጅመንት እንዲሁም በባለድርሻ አካላት እንዲገመገምና ለሰራተኞች ተዋውቆ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለስራው አስፈላጊ ግብዓቶችን የማሟላት፣ ስራዎችን የሚያሳልጡ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋትና የማጠናከር እንዲሁም የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመሰራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለደን ልማት እና ምርምር እንዲሁም ለአቅም ግንባታ ስራዎች 28,241,250 USD ከተለያዩ አጋር አካላት ማግኘት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከዛፍ ዘር ሽያጭ 496,390 ብር ተገኝቷል፡፡

በተደረገው የደን ልማትና ጥበቃ ስራ ከደን ዘርፍ 8 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ 13.1756 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መቀነስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100 % በላይ ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት ባለፉት ዓመታት በተደረገ የተጠናከረ የደን ተከላና ጥበቃ ስራዎች ነው፡፡

በደን ልማት፣ በደን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲሁም በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ2.05 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ ለ2.643 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች በስልጠናና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

2.4 ሚ/ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በ2.944 ሚ/ሄ/ር ከ100% በላይ መለየት ተችሏል፣ 10.67 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ

10.168 ቢሊዮን (የዕቅዱን 95.29%) የደን ችግኞች መትከል ተችሏል፡፡ የቀርቀሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ሄ/ር ለማድረስ 0.16 ታቅዶ ሚ/ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ 2.2 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ ለማስቻል ታቅዶ 1.977 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 89.86% ሆኗል፡፡

በየበጀት ዓመቱ 18.678 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በየዓመቱ 18.678 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ሆኗል፡፡ 2.28 ሚሄ/ር የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን እንዲታቀፉ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ 510 ሚሊየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተሰራው ስራ 665.7 ሚሊየን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ 100% በላይ ሆኗል፡፡ ከእቅድ በላይ የተከናወነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው፡፡ በተመሳሳይ በምርምሩ ዘርፍ የውስጥ ገቢን ጨምሮ ከአጋር አካላት በተገኘ ድጋፍ 2.4 ሚሊዮን ብር ማግኘት ተችሏል፡፡

ከ 2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ለ870,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፤ የደን ምርቶችን በመጫን፤ በማጓጓዝና በማውረድ፤ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፤ በእንጨት ኢንዱስትሪ፤ ኢንተርፕራይዞችና ማህበራትን በማደራጀት፤ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ በመቸርቸርና በመላክ ፤በከሰል ማክሰል (አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ 800,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 92% ነው፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 2.38 ሚልዮን ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ ክንውን 5.038 ሚልዮን ቶን (ከዚህ ውስጥ 25,000 ቶን ለውጭ ገበያ የቀረበ) ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት በዘርፉ  የደን ውጤት ምርት ፍላጎት እና አቅርቦት እየጨመረ በመምጣቱ ነው፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ተቋሙ በምርምር ዘርፍ የደን ሽፋን ለመጨመር ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የደን ውጤቶችን ምርታማነት ለማሳደግ፣ እሴት ለመጨመርና የገበያ ስርዓትን ለመዘርጋት እና ስርዓተ-ምህዳሩን ለማሻሻል የሚያስችሉ በሰዉ ሰራሽ ደን፣ በደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን፣ በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ፤ በተፈጥሮ ደን እና በአየር ንብረት ለወጥ የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን ነድፎ መረጃና ቴክኖሎጂዎችን በማዉጣት የበኩሉን ሀገራዊ ሃላፊነት ሲወጣ ቆይቷል፡፡ በዝርዝር ስንመለከት ከ2013 እስከ 2015 በጀት ኣመት አጋማሽ ድረስ በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 21 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61.8%፣ በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ 43 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 47 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100%  በላይ የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 32 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 27 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 84.4% እና በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 11 መረጃ ለማዉጣት ታቅዶ 10 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 90.9% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ያለዉን የስራ ክንዉን ስንመለከት በምርምሩ ዘርፍ 120 የምርምር ውጤቶችን (100 መረጃዎች 20 ቴክኖሎጂዎች) ለማውጣት ታቅዶ 105 የምርምር ውጤቶችን (95 መረጃዎች 10 ቴክኖሎጂዎች)  ለማውጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 87.5 % ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋትን በተመለከተ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ለ470 ከተለያዩ አካላት ለተዉጣጡ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ466 ተጠቃሚዎች ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 99.1% ነዉ፡፡

በአጠቃላይ 2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በተሰሩ ስራዎች የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም 93.3% ሲሆን፣ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛ በጀት 749,840,583.40 ብር ውስጥ 574,567,617.85 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 76.6 % ነው፡፡ አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት በዋናነት በሃገር ደረጃ በተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል የዋጋ

መናር እና በገበያ ላይ የግንባታ ማቴሪያል እጥረት ሳቢያ የሁለቱ ላቦራቶሪዎች የግንባታ ስራዎች በመዘግየታቸው ነው፡፡ ይህንም ችግር ለመቅረፍ ከተቋራጭ ድርጅቶቹ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል፡፡ ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 2. መግቢያ

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችንና ግልጋሎቶችን ያበረክታል፡፡ ደን ለማገዶ እና ለኮንስትራክሽን፣ የቤተሰብ ገቢን እና የሀራችንን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የአፈር ክለት ለመቀነስና ለምነትን ለመጨመር፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም፣ ለዱር እንስሳት መጠለያነት፣ በውሀ አካላት ላይ የሚፈጠረውን ደለል ለመቀነስ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ወዘተ የሚያበረክታቸው አስተዋጽኦዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ የደን ልማት በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም እንዲሁም በደን ምርምር ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ቀርፆ እንዲሁም የልማት ስራዎችን አቅዶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተጀመረው ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከክልሎች፣ ከተማ መስተዳድሮችና ከሚመለከታችው አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት መጠነ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሀይማኖት ተቋማት ጭምር እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ እያደገ ከመጣው የህዝብ ቁጥር ጋር ተያይዞ ለማገዶ እና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል የእንጨት ፍላጎት መጨመር፣ የደን ምንጣሮና የደን ቃጠሎ፣ ልቅ ግጦሽ እንዲሁም በየጊዜው የሚወጡ የህግ ማዕቀፎች በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ አለመሆን፣ የመሬት ፓሊሲና ዕቅድ አለመኖር እና ሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች በደን ሃብታችን ላይ ለሚደርሰው መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያቶች ናቸው፡፡

ይህንን ችግር ለማስቀረት በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ሲሆኑ ከእነዚህም ተግባራት መካከል የአስር ዓመት፣ የአምስት ዓመትና ዓመታዊ ዕቅዶች በማቀድ እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

የደን ሀብታችንን ከመመናመን ለመታደግና ሀገራችን ከተፈጥሮ ሀብቶቿ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ ለማስቻል በምርምሩ ዘርፍ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ወጥተዋል፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ደን ልማት ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት በደን ልማት እና ምርምር ዘርፎች የተከናወኑትን ዋና ዋና ተግባራትን አፈፃፀም አካቶ የያዘ ሲሆን ከ2013 እስከ 2014 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በሪፖርቱ ውስጥ ያለው አፈፃፀም

ቀደም ሲል ከነበሩት ሁለት የተለያዩ ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት ተቋማት ሪፖርት ላይ የደን ልማት እና የደን ምርምር ስራዎች አፈፃፀም ተወስዶ የተጠናቀረ ሪፖርት መሆኑን እየገለፅን ከዚህ ቀጥሎ በተገለፀው አግባብ የዋና ዋና ግቦች እና ተግባራት አፈፃፀም ቀርቧል፡፡

## 3. በቁልፍ የውጤት አመልካቾች (KPIs) ላይ የተመሰረተ ከ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የፊዚካል ስራ አፈፃፀም ትንተና

### ግብ 1.የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ

- በዘርፉ አገልግሎት ፈልገው የመጡትን ተገልጋዮችን በአገልግሎት አሰጣጥ እስታንዳርድ መሰረት በአግባቡ እንዲስተናገዱ ተደርጓል፡፡
- በተቋማችን የላብራቶሪ አሰራር፣ አደረጃጀትና የላብራቶሪ መሳሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ ለክልል የሥራ ሐላፊዎችና ባለሙያዎች ገለጻ እና ልምድ የማካፈል ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመመረቂያ ፅሁፍ ማሚያ እና ለኢንተርንሺፕ የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል እንዲሁም የሚፈልጉትን መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- ለግለሰብ፣ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች (በደን ልማት፣ አጠቃቀምና ጥበቃ እንዲሁም በምርምር) የማማከር አገልግሎቶች ተሰጥተዋል፡፡
- ከ27 የዛፍ ዝርያዎች የተሰበሰበ 1734.25 ኪ.ግ ዘር ለመንግስታዊ፤ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ለግል አልሚዎች ተሰራጭቷል፡፡
- ከተለያዩ አካላት ለቀረቡ የዛፍ ችግኝ የትብብር ጥያቄ የተለያዩ የሀገር በቀልና የውጭ ሀገር የዛፍ ዝርያዎችን ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### የተገኘ ውጤት

- የተገልጋይ እርካታ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ከ80% ወደ 84% ማሳደግ ተችሏል፡፡

ግብ 2. የሀብት አጠቃቀምና ዉጤታማነትን ማሳደግ

- የመንግስትን የፋይናንስ እና የግዥ መመሪያን መሰረት በማድረግ የተመደበ ንብረትና በጀትን በአግባቡ መጠቀምና ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል የድጋፍና ክትትል ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- ከ2013 እስከ በ2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በፌደራል ዋና ኦዲተር በተከናወነው የፋይናንስ እና የንብረት የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ በየበጀት ዓመቱ የማስተካከያ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ አፈፃፀሙ ላይ የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የዉስጥ ኦዲት በተያዘው ዕቅድ መሰረት በየሩብ ዓመቱ ተገቢው ክትትል ማድረግ ተችሏል፡፡
- የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማ እና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆን ለማስቻል ለተቋሙ ከመንግስት የተመደበውን በጀት አሳታፊ በሆነ መንገድ በፕሮግራም በጀት መርህ መሰረት ፕሮግራሞችን፣ ፕሮጀክቶችን፣ ዋና ዋና ተግባራት እና የሚያስገኙትን ውጤት ታሳቢ ያደረገ የበጀት ድልድል ስራ ተከናውኗል፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛና ካፒታል በጀት 749,840,583.40 ብር ውስጥ 574,567,617.85 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 76.6 % ነው፡፡ አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት በዋናነት በሃገር ደረጃ በተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል የዋጋ መናር እና በገበያ ላይ የግንባታ ማቴሪያል እጥረት ሳቢያ የሁለቱ ላቦራቶሪዎች የግንባታ ስራዎች በመዘግየታቸው ነው፡፡ ይህንም ችግር ለመቅረፍ ከተቋራጭ ድርጅቶቹ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል፡፡ ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

**በልማት አጋር አካላት ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የበጀት አፈፃፀም**

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በደን ምንጣሮና መመናመን የሚለቀቅ ሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ሴክሬታሪያት ደረጃ ብር 337,708,472.85 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 271,726,620.23 (80.5%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት ገንዘቡ ከድጋፍ ሰጭው በወቅቱ ስላልተለቀቀ ነው፡፡
- የደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት (FSTU) ብር 159,040,898.00 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ 117,443,013.20 (73.74%) መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ ያነሰበት ምክንያት ገንዘቡ ከድጋፍ ሰጭው በወቅቱ ስላልተለቀቀ ነው፡፡
- በደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም (FSDP) ብር 526,901,685.08 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 480,933,290.71 (91.28%) ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡
- የከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት ብር 31,598,915.03 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 31,598,915.03 (100%) ስራ ላይ ማዋል ተችሏል፡፡
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ደን ተኮር የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት (CRFL) 24,060,352.21 ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 19,276,175.92 (80.12%) ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

**የተገኘ ውጤት**

- የተመደበው በጀት በወቅቱና ለታለመለት ዓላማ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**ግብ 3- የሀብት ግኝትን ማሳደግ**

- የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለደን ልማት እና ምርምር እንዲሁም ለአቅም ግንባታ ስራዎች 2,282,795.00 ብር እና 28,241,250 USD ከተለያዩ አጋር አካላት ማግኘት ተችሏል፡፡
- ከዛፍ ዘር ሽያጭ 496,390 ብር ተገኝቷል፡፡
- ለቀጣይ የደን ልማትና ምርምር ስራዎችን አጠናክሮ ለማከናወን 110 ሚሊየን USD ሊያስገኙ የሚያስችሉ ሶስት ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ለአጋር አካላት ቀርበው በመገምገም ላይ ይገኛሉ፡፡

**የተገኘ ውጤት**

- መንግስት ከሚመድበው መደበኛ በጀት ባሻገር ተጨማሪ ሀብት ማግኘት ተችሏል፡፡

**ግብ 4፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል**

- ሀገር አቀፍ የደን ሽፋን መጠንን ለማስላት ሳተላይት ምስል ማውረድና የሞዛይክ (ወጥ የማድረግ) ስራ መስራት፣ ወካይ ናሙና (Training points) መሰብሰብ፣ የባዮሞች ቅርጽ (Vector file) ማስተካከል እና ማዘጋጀት፣ ረቂቅ እትም ካርታ/First Draft Map/ ማውጣትና የካርታውን የትክክለኛነት ልኬት/Accuracy Assessment/ የማረጋገጥ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- ከላይ የተጠቀሱ ስራዎችን በማከናወን በደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ስራዎች ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 13.1756 ሚሊዮን ቶን $CO_2e$ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነስ እንደተቻለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የአህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች ተሳትፎን በተመለከተ በአምስት መድረኮች ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ታቅዶ በስድስት መድረኮች ላይ ተሳትፎ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100 በላይ ነው፡፡ ከተከናወኑት መድረኮች መካከል ኒውዮርክ ላይ በተካሄደው የመንግስታቱ ድርጅት 77ኛው የስብሰባ መድረክ እና የ27ኛው ሻርም ኤል-ሼክ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ በመሳተፍ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ድርድር መድረኮች ይገኙባቸዋል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች**

- ከደን የሚቀነሰውና የሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን የስሌት ዘገባ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- በአለም ዓቀፍ መድረኮች የሃገራችንን ጥቅም ለማስጠበቅና ግንዛቤ ለመፍጠር ተችሏል፡፡

**ግብ 5፡- የደን ህግ ተከባሪነት ማጎልበት**

**1. የህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር**

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በደን ልማት፣በደን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲሁም በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ2.05 ሚሊዩን የማህበረሰብ ክፍሎች

ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ ለ2.643 ሚሊዩን የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል፡፡

- በደን ሃብት እሴት ጭማሪ እና በደን ኢንዱስትሪ ዙሪያ ከደን ኢንዱስትሪ ባለቤቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በዘርፉ ባሉ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች ዙሪያ ውይይት ተካሂዷል፡፡

## 2. በደን ላይ የሚደርሰውን ህገ ወጥ ተግባራትን መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በደን ውጤቶች ንግድ ለተሰማሩ 400 ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ446 ግለሰቦች የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነዉ፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር የተገኘ 122822.8 ሜ/ኩብ የተለያዩ የደን ውጤቶች፣ 106908.5 ኩንታል ከሰል፣ 169 ኩ/ል እጣንና ሙጫ፤945 ሜ/ኩብ የማገዶ እንጨት፣ 4,601 ሜ/ኩ አጣና፣ 212 ሜ/ኩብ ማገር (የቆርቆሮና የግድግዳ) ፣155 ሜ/ኩብ ፍልጥ፣ 571.54 ሜ.ኩብ የተለያዩ የጣውላ አይነቶች እና 10290 ሜ/ኩ ግንዲላዎች ተወርሷል፡፡ በህገ ወጥ ከተወረሱት የደን ምርት ዉጤቶቸ ሽያጭና ከቅጣት 6274000 ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ155 የደን ልማት ጥበቃና ቁጥጥር ግብረ-ሃይል የማቋቋምና የማጠናከር ስራ፣ 145 የደን ኬላዎች የማጠናከር ስራ እና 39 አዲስ የደን ኬላዎችን የማቋቋም ስራ ተከናዉኗል፡፡

- በህገ ወጥ መንገድ የደን ውጤቶችን በማዘዋወር እና የተፈጥሮ ደን መሬት ወረራ ተግባር ላይ በተሰማሩ 3950 ግለሰቦች ላይ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች ተወስዶባቸዋል፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በህገ-ወጥ የደን ዉጤት ማምረትና መሸጥ ስራ በተሰማሩ 248 ግለሰቦች ላይ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በህግ እንዲታይ ተደርጓል እንዲሁም 31 ባለሀብቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመወሰድ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የደን ግብረ ኃይል የማጠናከር ስራ የማጠናከር እና 26 የንግድ ፈቃድ እድሳት የመስት ስራ ተከናዉኗል፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የደን ውጤቶችን በህጋዊ መንገድ ለማዘዋወር 2400 ጥራዝ የይለፍ ፈቃድ መስጫ ደረሰኝ በማሰራጨት 64527 ህጋዊ የደን ውጤቶች ማዘዋወሪያ የይለፍ ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በኢንቨስትመንት ስም እና በአርሶ አደር ስም ከተሰጣቸው መሬት በላይ የተፈጥሮ ደን ውስጥ የገቡ ግለሰቦች ተከሰው እንዲወጡ በማድረግ 494.7 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪዎቹ ጉዳያቸው በክስ ተይዞ ይገኛል፡፡ እነዲሁም በህገወጥ መንገድ የደን መሬት ወረራ በተሰማሩ በ42 ግለሰቦች ላይ የ36600 ብር ቅጣት እና በእስራት እንዲቀጡ ተደርጓል፡፡
- በደን ውጤቶች ንግድ በተሰማሩ 6121 ነጋዴዎች ላይ በተደረገ ጥናት 3181 የብቃት ማረጋገጫ ያወጡና የደን ውጤቶች ንግድ ፍቃድ የተሰጣቸው ሲሆን ያለብቃት ማረጋገጫ የደን ውጤቶች ንግድ ፍቃድ ባወጡት ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ ተወስዷል፡፡

## 3. የደን ህግ ማዕቀፍ ዝግጅትን በተመለከተ

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ 1065/2010 ማስፈፀሚያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡
- የከተሞች የደን አያያዝ ረቅቅ ደንብ ለማዘጋጀት በረቂቅ ደንቡ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮችን በመለየት የመጀመሪያ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች**

- የህብረተሰቡ ግንዛቤ ተሻሽሏል፣
- የህግ ተከባሪነትን ለማረጋገጥ የተሻለ ጥረት ተደርጓል፡፡

## ግብ.6 - አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ

### ተግባር 1. የሰው ሰራሽ ደን ልማት

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተከናወነ ስራ እና በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ የተከላ መሬት ልየታ፣ ችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ  የሚከተሉት ስራዎች ተከናውነዋል (ሰንጠረዥ 1 እና 2)።

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 2.4 ሚ/ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በ2.24 ሚ/ሄ/ር ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 93.16% ።
- 10.67 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 10.168 ቢሊዮን (የዕቅዱን 95.29%) የደን ችግኞች መትከል ተችሏል።
- የቀርቀሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ሄ/ር ለማድረስ 0.16 ታቅዶ ሚ/ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው። አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው።
- ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ለስምንት ቀርከሃ ውጤቶች ደረጃ ተዘጋጅተዋል።

**ሠንጠረዥ 1. የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮች የሰው ሰራሽ ደን ልማት አፈጻጸም (ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ)**

| ክልል/የከተማ አስተዳደር | የተተከለ ችግኝ በሚ/ቁጥር | በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር | ከተተከለው ጠቅላላ የደን ችግኝ ውስጥ የቀርከሀ ችግኝ መጠን በሚ/ቁጥር | **እንክብካቤ የተደረገለት የተከላ መሬት በሄ/ር** |
|---|---|---|---|---|
| አማራ | 2,585.940 | 256,799.80 | 1.460 | 596,648.20 |
| ኦሮሚያ | 5,165.230 | 1,303,314.62 | 64.420 | 962,956.16 |
| ደብብሕ | 1,869.773 | 483,388.50 | 6.993 | 272,864.35 |
| ሲዳማ | 325.541 | 54,400.21 | 23.450 | 84,828.90 |
| ደ/ምዕ/ኢት | 99.920 | 26,472.79 | 3.910 | - |
| ቤ/ጉሙዝ | 93.474 | 55,732.36 | 8.000 | 8,381.24 |
| ጋምቤላ | 5.753 | 8,122.00 | 0.130 | 59,944.00 |
| አፋር | 4.300 | 590.00 | 0.000 | - |
| ሶማሌ | 3.458 | 2,268.06 | 0.000 | 3,866.11 |
| ሐረሪ | 2.358 | 605.36 | 0.000 | 416.00 |
| ድሬዳዋ | 1.842 | 2,007.00 | 0.042 | 508.20 |
| አዲስ አበባ | 11.138 | 750,899.99 | 0.012 | 296.00 |
| ድምር | 10,168.727 | 2,944,600.69 | 108.416 | 1,990,709.16 |

**ሠንጠረዥ 2. በሰንጠረዥ 1 ከተገለፀው ውስጥ የፕሮጀክቶች ተሳትፎ በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር (ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ)**

| **የፕሮጀክቶች ተሳትፎ** | **በተከላ የተሸፈነ መሬት መጠን በሄ/ር** |
|---|---|
| የደን ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም | 71,731.23 |
| በአዳፕቴሽን ፈንድ ፕሮጀክት | 2,845.74 |
| በደን ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዩኒት | 6,001.90 |
| በKFW ደን ልማትና ብዝሃ ሕይወት እንክብካቤ ፕሮጀክት | 1,456.19 |
| CRFL (የDANIDA ድጋፍ) ፕሮጀክት | 3,322.30 |
| በአውሮፓ ህብረት በሚደገፍ ፕሮጀክት | 4,461.96 |
| በከፍታማ ቦታዎች የአየር ንብረት ለዉጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት | 40,928.62 |
| **ድምር** | **130,747.94** |

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በደን ችግኝ ከተሸፈነው 2,944,600.69ሄ/ር ውስጥ **130,747.94 ሄ/ር** (4.4%) የተሸፈነው በፕሮጀክቶች ድጋፍ ነው፡፡

- በሁለት ዓመት ተከል ጊዜ ውስጥ አንድ የደን ሽፋን መረጃ ለማውጣት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት መረጃውን ማውጣት ተችሏል፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 775 ቶን የዛፍ ዘር ለማሰባሰብና ለማሰራጨት ታቅዶ 1,249.32 ቶን በማከናወን አፈጻጸሙን ከ100% በላይ ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅዱ በላይ የሆነበት ምክንያት በመደበኛ ስራ ከተከናወኑት በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና አጋር አካላት ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

- ፖሊቲን ቲዩብ አቅርቦትን በተመለከተ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተከናወኑ ስራዎች 14,662.05 ኩ/ል ማከናወን ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 3. በክልል/የከተማ አስተዳደር የተሰራጨ የደን ዘር (በቶን)፣ፖሊቲን ቲዩብ (በኩ/ል)**

| ተ.ቁ | ክልል | የደን ዘር በቶን | ፖሊቲን ቲዩብ በኩ/ል |
|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | 248.15 | 7,181.20 |
| 2 | ኦሮሚያ | 721.00 | 3,806.22 |
| 3 | ደብብሕ | 184.42 | 569.85 |
| 4 | ሲዳማ | 34.44 | 2,182.18 |
| 5 | ደ/ምዕ/ኢት | 8.79 | 68.50 |
| 6 | ቤ/ጉሙዝ | 15.25 | 27.93 |
| 7 | ጋምቤላ | - | - |
| 8 | አፋር | - | - |
| 9 | ሶማሌ | 2.30 | 719.42 |
| 10 | ሐረሪ | 1.10 | 48.00 |
| 11 | ድሬዳዋ | 2.38 | 58.74 |
| 12 | አዲስ አበባ | 21.50 | - |
| 13 | በደን ምርምር | 10.00 | - |
| | ድምር | 1,249.32 | 14,662.05 |

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በ19 ከተሞች የደን አያያዝ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ18 ከተሞች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ የተደረገላቸው ድጋፍ

በችግኝ ጣቢያ ዝግጅት እና አያያዝ፤ በተከላ ቦታ ዝግጅት፣ በተተከሉ ችግኞች የእንክብካቤ ሁኔታ (የአረምና ኩትኳቶ፤ ውሃ ማጠጣት) ይገለፃል፡፡

- እ.ኤ.አ ከ2018 እስከ 2022 ያለውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የREDD+ ፕሮጀክት የ59 ወረዳዎች (24 ወረዳዎች ኦሮሚያ፣ 29 ወረዳዎች ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ 6 ወረዳዎች ጋምቤላ) የደን ሽፋን ለውጥ መረጃ የሚያሳይ የIPCC የመሬት አጠቃቀም መስፈርትን መሰረት ያደረገ የመጀመርያ ረቂቅ እትም ካርታ ከፍተኛ ጥራት ባለው የሳተላይት ምስል በመጠቀም ማውጣት ተችሏል፡፡
- የሰው ሰራሽ ደኖች በሄ/ር ያላቸውን ምርታማነት እና የካርበን ክምችት መጠን የሚገልፅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል (ሠንጠረዥ 5)፡፡

**ሠንጠረዥ 4. የክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮች ምርታማነት (ሜ.ኩ/ሄ/ር እና የካርበን ክምችት)**

| ክልል | ምርታማነት በ(ሜ.ኩ/ሄ/ር) | ባዮማስ (ቶን/ሄ/ር) | የካርበን ክምችት (ቶን/ሄ/ር) |
|---|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 134.926 | 104.2560 | 49.0003 |
| አማራ | 383.781 | 235.2770 | 110.5802 |
| ኦሮሚያ | 389.294 | 201.2891 | 94.6059 |
| ሲዳማ | 542.514 | 304.8161 | 143.2635 |
| ደቡብ | 403.171 | 254.0901 | 119.4224 |

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በአንደኛው ዙር ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ 60 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 25 በመቶ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ 41.6 በመቶ ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በፀጥታ ችግር እና ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት በጀት በወቅቱ ባለመለቀቁ ምክንያት ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ የሚከተሉት የዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

- ✓ የደን ቆጠራ የመስክ ማኑዋል (Forest Inventory Field Manual) በአዲስ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ የመስክ መረጃ መሙያ ቅፅ (Field Form) ተዘጋጅቷል፡፡
- ✓ የደን ቆጠራውን (Forest Inventory) ለማከናወን የሚረዱ ወካይ ናሙናዎችን 1881 ኮኦርዲኔቶች (Sample point XY Coordinates) ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጂ አይ ኤስ ሶፍትዌር በመጠቀም ተዘጋጅተዋል፡፡

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ  የደን ማኔጅመንት ፕላን ለ 0.4 ሚ/ሄ/ር ደኖች እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ታቅዶ በአጠቃላይ ለ1.165 ሚ/ሄ/ር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው፡፡

**ተግባር 2. የደን ጥበቃ ማካሄድ**

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 18.68 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ስራ ለማከናወን ታቅዶ 18.68 ሚሊዮን ሄ/ር (100%) ተከናውኗል፡፡
- በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የደን መሬት ላይ ተከስቶ የነበረውን የደን እሳት ቃጠሎ ህብረተሰቡን፣ አመራሩን፣ ባለሞያውንና የፀጥታ አካሉን በማስተባበር በጋራ በተደረገ ርብርብ እሳቱን በቁጥጥር ስር የማዋል ስራ ተሰርቷል፡፡
- በደን ላይ ሊደርስ የሚችለውን የደን እሳት የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት “MyDewetra” የሚባል ፕላት ፎርም አማካኝነት የሙከራ ትግበራ ማለትም የየእለቱን ምልከታና የየሶስት ቀናት ትንበያን በመጠቀም እስካሁን 191 የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃው ለክልሎችና ለሌሎች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግ ተችሏል፡፡
- በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች ላይ (ለምሳሌ ዶቅማ እና ካቻ ግራር) የማይታወቅ ተባይ ተነስቶ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ያለውን ነፍሳተ ተባይ ለመቆጣጠር ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር መከላከል የተቻለ ሲሆን ጉዳት አድራሹን ነፍሳተ-ተባይ ምንነትና የዕድገት ዑደት ልየታ ጥናት ተሰርቷል፡፡

**ተግባር 3 ፡- የተራቆቱ ደኖችና መሬቶችን መለየት፣ መከለልና ማልማት**

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ 2.2 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ ደኖችና መሬቶችን የመለየት፣ የመከለልና የማልማት ሥራ ታቅዶ 1.977 ሚ/ሄ/ር የዕቅዱን 89.86% ማከናወን ተችሏል፡፡

**የተገኘ ውጤት**

- ጥራታቸውን የጠበቁ የደን ችግኞችን የማዘጋጀት፣ የመትከልና እንክብካቤ ስራ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡
- በደን ማኔጅመንት ፕላን የተመሩ የደን ይዞታዎች ሽፋን ጨምሯል፡፡
- በደን ላይ  ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ተችሏል፡፡

## ግብ 7. የደን ሃብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣

- ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ድረስ በ2.28 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖችን አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በአጠቃላይ በ1,238 የአሳታፊ ደን አስተዳደር ማህበራት ለተደራጁ ለ258,931 (ወንድ 213,358 እና ሴት 45,573) የማህበሩ አባላት በአሳታፊ ደን አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡
- ከ 2013 እስከ 2015 ግማሽ ዓመት ለ870,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፤ የደን ምርቶችን በመጫን፤ በማጓጓዝ በማውረድ፤ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፤ በእንጨት ኢንዱስትሪ፤ ኢንተርፕራይዞችንና ማህበራትን በማደራጀት፤ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ በመቸርቸርና በመላክ፤ በከሰል ማክሰል (አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ800,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 92% ነው፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 ግማሽ ዓመት 510 ሚሊዮን ብር ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 665.7 ሚሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው፡፡
- ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰልን በተመለከተ ከ2013 እስከ 2015 ግማሽ ዓመት ድረስ 0.467 ሚልዮን ቶን ለማቅረብ እቅድ ተይዞ 0.6984 ሚልዮን ቶን የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከፍ ያለበት ምክንያት በአማራ ክልል በአርሶ አደሩ ይዞታ በከፍተኛ ሁኔታ ተመርቶ ለገበያ ስለቀረበ እና የገቢ ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ድረስ 2.38 ሚልዮን ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ 5.038 ሚልዮን ቶን የቀረበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት የደን ምርት ውጤቶች ፍላጎት እና አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ ነው፡፡
- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ (Import Substitution) የውጭ ምንዛሪ መጠን

47 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ 22.124 ሚሊየን ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ 47.1% ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የደን ምርት ውጤቶች በተለይም የባህር ዛፍ አጣና እና እጣንና ሙጫ የሚመረትባቸው አካባቢዎች ላይ የፀጥታ ችግር በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

- ከ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የደን ኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች ያለባቸውን ችግሮች የመለየት ስራ በመስክ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡ የተለዩ ችግሮችን በተመለከተ የአመለካከት ችግር፣ የሃይል መቆራረጥ፤ የመለዋወጫ እጥረት፣ የገበያ ትስስር ችግር፣ የግብዓት አቅርቦት ዕጥረት እና የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ለመለየት ተችሏል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን በአሳተፊ ደን አስተዳደር በማስገባት የአካባቢውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ የደን ምርት ዕድገት ታይቷል፡፡
- ለዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

**ግብ 8፡- መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ**

- በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 21 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 61.8% ነዉ፡፡ አፈጻፀሙ ያነሰበት ምክንያት መረጃዎችን ለማውጣት ተጨማሪ ጊዜ በማስፈለጉ፣ የአንዳንድ የሙከራዎች ውጤታማ አለመሆን፣ ከፀጥታ መደፍረስ ጋር ተያይዞ በቂ ክትትልና እንክብካቤ ባለመደረጉ፣ በተፈጥሮ ክስተት፣ በአጥር መፍረስና በችግኞች መወሰድ፣ ከልቅ ግጦሽ ጋር ተያይዞ እንዲሁም በሰፈራና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የምርምር ስራዎች የሚያስቀጥል ቁመና እንደሌላቸውና እንዲቋረጡ ስለተወሰነ ነው፡፡
- በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ 43 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 47 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% በላይ ነዉ፡፡
- የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 32 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 27 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 84.4% ነዉ፡፡

- በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 11 መረጃ ለማዉጣት ታቅዶ 10 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 90.9% ነዉ፡፡
- በአጠቃላይ ከ2013-2015 ዓ.ም በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በሁሉም የምርምር ዘርፎች 120 የምርምር ቴክኖሎጂዎችንና መረጃዎችን ለማዉጣት ታቅዶ 105 ዉጤቶችን ማዉጣት ተችሏል አፈፃፀሙም 87.5 ነዉ፡፡

**ግብ 9፡- መረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ**

**የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ሥራ ሲከናወኑ የቆዩትን ከዉጭ የገቡ የቀርከሃ ዝርያዎች በመስክ ላይ ያለበት ደረጃ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጅ አቀባበል መገምገም ተችሏል፡፡
- በቅድመ ማስፋፋት ሥራዎች ላይ ቴክኖሎጂዎችን ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ለተጠቃሚዎች በማድረስ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡
- የወጡ የምርምር ውጤቶችን በበይነ-መረብ ላይ በመጫን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- ከ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በምርምር የወጡ 24 መረጃዎችን በተለያዩ mainstreaming የሚዲያ ቻናሎች ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 24ቱንም ተደራሽ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% **ነዉ፡፡**
- ከ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በምርምር ለወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች 34 የትግበራ ፓኬጅ ለማዘጋጀት በእቅድ ተይዞ ለ34 ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100%፡፡
- በፖሊሲና ሶሺዮኢኮኖሚክስ 2፣ በሰዉ ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን ምርምር 4፣በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ ምርምር 1 በድምሩ 7 የምርምር ውጤቶችን በታወቁ ጆርናሎች ላይ ታትመዋል፡፡
- በደን ልማት ስራዎች ዙሪያ የተዘጋጁ የዜና ስርጭቶች ላይ ለህብረተሰቡ እንዲተላለፉ በተለያዩ የሚዲያ ቻናሎች በድግግሞሽ እንዲሰራጩ በማድረግ ተደራሽነታቸውን ማስፋት ተችሏል፡፡

➢ የምርምር ስራዎች በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ስለሚሰራው የምርምር ስራ እና ጠቀሜታው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡
➢ ከዚህ በፊት መረጃቸው ወደ ዛፍ ዘር ምንጮች የመረጃ ፖርታል ቋት ያልገቡ 40 የዛፍ ዘር ምንጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ፖርታል ቋት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 5. ለቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች በማስተዋወቅ ስራ ላይ የተሰጡ ስልጠናዎች አፈጻጸም**

| የሥልጠና ዓይነት | ወ | ሴ | ድምር |
|---|---|---|---|
| በተመረጡ የእንጨት ዝርያ ባህርያት፣ ስለአሰነጣጠቅ ዘዴዎች እና አደራረቅ እንዲሁም እንጨትን እንዴት ለተለያዩ አገልግሎት መጠቀም እንድሚቻል የንድፈ ሀሳብና የትግበራ ስልጠና | 32 | 6 | 38 |
| ለአርሷደሮች እና የግብርና ባለሙያዎች ከውጭ የገባ የቀርከሃ ዝርያ ማላመድ ለይ የግንዛቤ ማስጨበጫና የማጠናከሪያ ስልጠና | 91 | 19 | 110 |
| በአፋር አሚባራ ወረዳ ለሚገኙ ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ለተመረጡ ከፕሮሶፒስ ጁሊፍሎራ ለሀይል ምንጭነት (Briquete) ማዋል | 20 | 6 | 26 |
| ድምር | 143 | 31 | 174 |

**የተገኙ ውጤቶች**

➢ ቴክኖሎጂዎችንና መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በማስተዋወቅ ግንዛቤ መፍጠርና ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ግብ10፡- የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣**

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ለ 0.2725 ሚሊዮን ሴቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 0.2353 ሚሊዮን የስራ እደል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙም 86.3% ነው፡፡ እንዲሁም ለ 0.4 ሚሊዮን ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 0.4667 ሚሊዮን ወጣቶች የስራ እደል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

በዘርፉ ሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል በማግኘት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣

### የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ማዕከል G+3 ላብራቶሪ ኮምፕሌክስ ግንባታ 60% ለማድረስ ታቅዶ አሁን ግንባታው ያለበት ደረጃ 45.13 % ሲሆን ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ምክንያት ተቋራጩ የፊኒሺንግ ዕቃዎችን በገበያ ላይ ያለማግኘት እና በዋጋ ንረት ምክንያት ነው፡፡
- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል B+G+5 ላብራቶሪ ኮምፕሌክስ ግንባታን 40% ለማድረስ ታቅዶ አሁን ግንበታው ያለበት ደረጃ 23.60% ነው፡፡ ለፕሮጀክቱ አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ምክንያት ተቋራጩ የግንባታ ግብዓቶችን በተለይም የሲሚንቶና የአርማታ ብረቶችን በሚያስፈልገው መጠን በገበያ ላይ ያለማግኘት እና በዋጋ ንረት ምክንያት ነው፡፡
- ተገልጋይን መሰረት ያደረገ የLAN ማስፋፊያ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የIFMIS እና የIBEX ተጠቃሚ ክፍሎች ሰርቨሮችን ተደራሽ ማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ለ 371ሄ/ር ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል፡፡
- የብሄራዊ የዛፍ ዘር ምንጮችን መመዝገቢያ (National Tree Seed Sources Registry Portal) ዌብ ፖርታልን በ 'https://www.national-tssr.gov.et' የድረ ገፅ ስያሜን ከኢትዮ ቴሌኮም በመግዛት፤ የ secutity configuration ስራ በማሰራት ወደ ዓለማቀፍ የመረጃ መረብ የማስገባት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ለማዕከላት የኔትወርክ መሳሪያዎች በRemote desktop connection system የኮንፊገሬሽን እና የጥገና ስራዎች ተሰርተዋል፤
- የተቀናጀ የሲቪል ሰርቭስ መረጃ ስርዓትን /icsmis.ecsc.gov.et/ በመጠቀም የሰራተኞችን የሰው ሀብት መረጃ /data/ ወደ መረጃ ማጠራቀሚያ ቋት በማስገባትና የሰው ሀብት አስተዳደር ስራዎችን ሙሉ በሙሉ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ ስርዓትን /Portal system/ በመጠቀም እንዲሰሩ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

**የተገኙ ውጤቶች፡-**

የተቋሙ መሰረተ ልማት እየተጠናከረ ይገኛል፡፡

## ግብ 12፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ

በዚህ ግብ ስር ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- ለ517 (ወንድ 347 እና ሴት170) የተቋሙ ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን፣ የምርምር እና አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚያሳልጡ የተለያዩ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡
- የረጅም ጊዜ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተመራማሪዎች፣ የልማትና የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞች በመጀመሪያ ዲግሪ 1 ወንድ፣ በሁለተኛ ዲግሪ 48 (39 ወንድ እና 9 ሴት)፣ በሶስተኛ ዲግሪ 24 (22 ወንድ እና 2 ሴት)፣ በጠቅላላ 73 (62 ወንድ እና 11 ሴት) ሰራተኞች ተገቢው ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡
- አለም አቀፍ የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ቀን፣ አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን እና የነጭ ሪባን ቀን አስመልክቶ ተለያዩ ዝግጅቶች በማቅረብና አስተማሪ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ለሠራተኞች የግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡
- በICSMIS, IFMIS እና eGP ዙሪያ ለተቋሙ ሰራተኞች የአጠቃቀም ስልጠና የመስጠት እና የስራ ላይ ድጋፍ ማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከፌደራል እና ከክልል ከባለድርሻ አካላት ለተዉጣጡ የማህበረሰብ ተወካዮች በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ለ18,719 (ወንድ 7,868 እና ሴት 10,851) የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡
- በተለያዩ ክልሎች በአሳታፊ ደን አስተዳደር በማህበራት ለታቀፉ 4,342 (1691 ሴት) የማህበራት አባላት ገቢያቸውን ለመጨመር የሚያስችሉ የተለያዩ ግብዓቶች ማለትም 387 ዘመናዊ ቀፎ፤ 79 ኪሎ ግራም የጓሮ አትክልት ዘር፤ 10 የጋዝ ማብላያ፤ 618 ሶላር ፓኔል፤ 1,390 በግና ፍየል፤ 13,425 ዶሮ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

### የተገኘ ውጤት

- የፈጻሚውንና የአስፈጻሚውን አቅም በማሳደግ የዘርፉን የተግባራት አፈጻም ማቀላጠፍ ተችሏል፡፡

## 4. የለውጥና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በየበጀት ዓመቱ የተቋሙ የአበይትና ቁልፍ ተግባር ዕቅድ አፈፃፀም የዋናው መስሪያ ቤትና ማዕከላት አመራሮች በተገኙበት ግምገማ ተካሂዶ የበለጠ መጠናከር በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ግብአት በመስጠት የቀጣይ የአሠራር አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡
- ተቋማዊ የቁልፍና አበይት ተግባራት የBSC /ባላንስድስኮር ካርድ/ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት እና ማዕከላት ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- የለውጥና መልካም አስተዳደር ሥራዎችን ቀጣይነት ለማጠናከር በየዓመቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን የማሟላት የሰው ኃይል ፍላጐት፣ የግዥ ፍላጐት እና የበጀት ፍላጐት ዕቅዶችን እንዲሁም የስልጠና ፍላጐት በማዘጋጀት አፈፃፀሙን የመከታተል ስራ ተሰርቷል፡፡
- ተቋማዊ የውስጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ዋና መንስዔዎች ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ዋና ዋና ጉዳዮች /ከአደረጃጀት፣ ከአሠራር ፣ ከማስፈፀም አቅም/ አንፃር በመለየት የመፍትሄ ሀሳቦችን ያካተተ ዕቅድ በማዘጋጀት የቀጣይ የአገልግሎት አሠጣጥ ለማሻሻል የሚያመላክት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡
- የኮሮና ቫይረስን /COVID 19/ ለመከላከል የሚያስፈልጉ ጥራታቸውን የጠበቁ ቁሳቁሶች፣ ግብዓቶችና ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉ ተደርጓል፣
- ሠራተኞች በተለያዩ ጊዜያት ስለ አገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች የመወያየት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ከመሥራቱም በላይ ነጩ ፖስታ ለነጩ ቤተመንግሥት በሚል መሪ ቃል ለአሜሪካ መንግሥት ፖስታ የመላክ ስራ ተሳትፈዋል፡፡
- በተቋማዊ የለውጥ ስራዎች አስመልክቶ አንድ የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል፡፡
- የዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን በማክበር አስተማሪ መልዕክቶችን የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡

## 5. የኦዲት ግኝት ምልከታ

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በተከናወኑ ኦዲቶች ላይ የበላይ አመራርን ያካተተ የኦዲት መውጫ ስብሰባ ውይይት በማድረግ በአሰራር ላይ የተፈጠሩ ክፍተቶች እንዲታረሙና በቀጣይ ስራ ግልፅነት እንዲፈጠር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፤ በማዕከላት

በመገኘት የኢንስፔክሽንና ክትትል ስራዎች ተሰርቷል፤ የንብረትና ሂሳብ ምዝገባ ወቅታዊነት የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 5. የኦዲት ግኝቶችና የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች**

| ተ.ቁ | የኦዲት ግኝት | የተወሰደ የማስተካከያ ርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | በሂሳብ መደብ 6172202 ያልተከፈለ ሂሳብ ብር 9872.(ከ02/12/2011 ዓ.ም) ጀምሮ የሚታይ መሆኑ | ለሚመለከታቸው አካላት ደብዳቤ በመፃፍ ተገቢው ማስተካከያ በማድረገግ ላይ ይገኛል፡፡ |
| 2 | ኢት 4-1330 የሆነ ሞተር ሳይክል ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የብቃት ማረጋገጫ የቴክኒክ ምርመራ ያላደረገ እና ያልታደሰ መሆኑን፣ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ | የቴክኒክ ምርመራ ተከናውኗል |
| 3 | በንብረት ክፍል ገቢ ሳይደረግ በአደራ በንብረት ክፍል የተቀመጠ ብዛት 1 ፍሪጅ፣ 1 ዩንቨርሳል ኦቨን፣ 1 heavy imqage analyzer፣ 1 scan copy analyzer እና ብዛት 9 ኩንታል እጣን መገኘቱ በኦዲት ተረጋግጧል፤ | በአደራ የተቀመጡ ንብረቶች ገቢ ተደርገዋል፤<br>በአደራ የተቀመጠ እጣን አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ |
| 4 | የተለያዩ ያገለገሉ እቃዎች በተመለከተ ብዛት 22 ቦክስ ፋይል፣ ብዛት 3 ፕሪንተር፣ ብዛት 6 ዲስክቶፕ ኮንፒውተር፣ ብዛት 2 ቶነር እና ካልኩሊተር ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፣ | የተገለፁት ንብረቶች ከስቶር ወጭ ተደርገው አገልግሎት ላይ ውለዋል፤ |
| 5 | እስቶክ ካርድ ያልተከፈተለት/ ንብረት መኖሩ | እስቶክ ካርድ እንዲከፈት ተደርጓል፡ |
| 6 | ከዘር ሽያጭና ከተለያዩ ገቢ ብር 526,304.55 ገቢ ያልተደረገ መሆኑን | ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበው ብር 413,438.88 ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ሂሳብ ተዛውሮ ማስረጃው ተያይዟል፡፡ ቀሪው ብር 112,865.67 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለገንዘብ ሚንስቴር ፈሰስ ተደርጓል፡፡ |
| 7 | ለደን ምርምር ላብራቶሪ ግንባታ በኢንቮይስ ቁጥር 5625 የተከናወነ የደን ምርምር ላብራቶሪ ግንባታ ፕሮጀክት ክፍያ ብር14,866,956.44 የተከፈለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለብር 1,189,356.52 የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተቆረጠ መሆኑ | ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ |
| 8 | ማስረጃ ያልቀረበበት ወይም በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ክፍያና ያልተወራረደ ሂሳብ ብር 158,071.977.00 መኖሩን፤ | 21,961,663.78 ለግንባታ ከተከፈለው ቅድመ ክፍያ የተወራረደ ሲሆን ቀሪው ብር 135,715,101.60 ለሁለት ግንባታ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለና በየክፍያው እየተቀረጠ ተመላሽ የሚደረግ፣ 353,684.12 ከመቀሌ ማዕከል የሚፈለግ ብር 41,527.50 ከተለያዩ ግለሰቦችና ሰራተኞች በመርሀ ግብር ተይዞ ወደፊት የሚሰበሰብ ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | በተቋሙ የሚወገድ ንብረቶች ለማስወገድ የሚደረገው እንቅስቃሴ በሚፈለገው መጠን ያለመሆን | አገልግሎት የማይሰጡ ተሽከርካሪዎች ተወግደዋል፡፡ |

## 6. የተቋሙ የፋይናንስ/ በጀት አፈፃፀም

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛና ካፒታል በጀት 749,840,583.40 ብር ውስጥ 574,567,617.85 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 76.6 % ነው፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስ ዋነኛ ምክንያት በዋናነት ለሁለት ግንባታዎች በሃገር ደረጃ በተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል የዋጋ መናር እና በገበያ ላይ የግንባታ ማቴሪያል እጥረት ሳቢያ የግንባታ ስራዎቻችን በመዘግየታቸው ነው፡፡ ይህንም ችግር ለመቅረፍ ከተቋራጭ ድርጅቱ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል፡፡ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄያችንን የተቀበለው በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 7. የክትትል እና ግምገማ አፈፃፀም

- ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የየበጀት ዓመቱን ዕቅድ በቢኤስ ሲ መሰረት ተዘጋጅቶ በማኔጅመንትና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገምግሞ ለሰራተኛው በማስተዋወቅ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- በየሩብ ዓመቱ በማኔጅመንትና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ አፈፃፀሙ እየተገመገመ ተመርቷል፡፡
- ማኔጅመንቱ በየ15 ቀኑ የተግባራትን አፈፃፀም እየገመገመ መርቷል፡፡
- በመስክ የሙያ ድጋፍ ለክልሎች ተሰጥቷል፡፡
- የአፈፃፀም ግብረ-መልስ ለክልሎች ተሰጥቷል፡፡

## 8. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጣሙ ችግሮችና የተወሰዱ/ሊወሰድ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች

- በክልሎችና ከዚያ በታች ባለ የአስተዳደር እርከን ወጥና የተጠናከረ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖር፣
- የተሟላ ሪፖርት ከክልሎች በወቅቱና ጥራት ባለው ደረጃ ማግኘት አለመቻል፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየጨመረ የመጣ የደን እሳት፣ የደን ተባይና በሽታ ክስተት፣
- የፀጥታ ችግር፣
- በCOVID-19 ወረርሺኝ ምክንያት የልማትና ምርምር ስራዎች በሚጠበቀው ደረጃ መፈፀም አለመቻሉ፤
- የምርምርና የልማት ስራዎችን ለማከናወን የበጀት ዕጥረት መኖሩ፣
- በግንባታ ዕቃዎች ዕጥረትና ዋጋ መናር ምክንያት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ አለመቻላቸው፡፡
- የልማት አጋር አካላት ድጋፍ በተጠበቀው ደረጃ አለመሆን፣

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ባለው ውሱን በጀት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ስራዎች በመለየት መስራት፣
- የዋጋ ማሻሻያ እንዲፈቅድልን የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ተጠይቆ የፈቀደልን ሲሆን በቀጣይ  የዋጋ ማሻሻያው ተግባራዊ ሲደረግ የግንባታ አፈፃፀሙ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

## 9. ማጠቃለያ

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም ጥረት የተደረገ ሲሆን አዲሱን የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመሰራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ከዳር ለማድረስ አመራሩ እና ፈፃሚው በጋራ ተረባርቦ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም የሁለት ዓመት ተኩል የፊዚካል ስራ አፈፃፀም ላይ ያጋጠሙን ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት እንዲሁም በቀጣይ ቀሪ ስራዎችን በዕቅዱ መሰረት በውጤታማነት ለመፈፀም እና የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ጠንክሮ መስራት ይጠበቃል፡፡

## 10.ዕዝል

### ዕዝል 1፡ የ2013-2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የልማት ዕቅድ አፈፃፀም በቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃ ፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንው ን | አፈፃፀ ም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 80 | 100 | 86 | 81.2 | 94.4 | 88 | 84 | 95 | 90 | 86 | 84 | 97.6 | 86 | 84 | 97.6 |
| ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ድርሻ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 88.4 | 88.4 | 100 | 91.9 | 91.9 | 100 | 100 | 91 | 91 | 100 | 90.43 | 90.43 |
| የተደረገ የውስጥ ኦዲት ክትትል | በቁጥር | 4 | 40 | 4 | 4 | 100 | 4 | 3 | 75 | 4 | 2 | 2 | 100 | 10 | 9 | 90 |
| የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር | በቁጥር | 1 | 10 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | | 200 | 50 | 302.23 | 100 | 20 | 138.2 | 100 | 20 | 20 | 28.2 | 100 | 90 | 468.63 | 100 |
| ግብ 4 ፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ከደን ዘርፍ የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ሜ/ቶን | 10.9 | 120 | 3 | 2.8 | 93.3 | 5 | 10.02 | 100 | 7 | | 0.35 56 | | 8 | 13.175 6 | 100 |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃ ፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንው ን | አፈፃፀ ም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተሳትፎ የተደረገባቸው አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች | ቁጥር | 1 | 20 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 | 2 | 1 | 2 | 100 | | | |
| ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የተዘጋጁ የደን ህግ ማዕቀፎች | በቁጥር | | 7 | | | | | | | 4 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት፣ | በሚሊዮን ቁጥር | | 20.05 | 2 | 2.1 | 100 | 0.05 | 0.439 | 100 | 2.5 | | 0.104 | | 2.05 | 2.643 | 100 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | በቁጥር | 659 | 1240 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 400 | 200 | 246 | 100 | 400 | 446 | 100 |
| ግብ 6 ፡- አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የዛፍ ዘር ማሰባሰብና ማሰራጨት | ቶን | 1958.59 | 3500 | 300 | 451.16 | 100 | 325 | 504.83 | 100 | 325 | 150 | 293.1 | 100 | 775 | 1249.32 | 100 |
| በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻ | በመቶኛ | 15.5 | 30 | 17 | 17.2 | 100 | 18.5 | 17 | 91.9 | 20 | | | | 18.5 | 17 | 91.9 |
| የተዘጋጁ የዛፍ ችግኞች | ቢ/ቁጥር | 18.735 | 40 | 4 | 6.52 | 100 | 4 | 3.799 | 95 | 3 | 0.25 | 2.763 | 100 | 8.25 | 10.67 | 100 |
| የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን (ከደን እሳት፣ ከተባይና በሽታ፣ ከመጤ ወራሪ አረም፣ ከህገወጥ ምንጣሮ እና መመናመን) | በሚ/ሄ/ር | 17.2 | 33.12 | 17.2 | 19.47 | 100 | 18.68 | 18.68 | 100 | 18.68 | 18.68 | 18.68 | 100 | 18.68 | 18.68 | 100 |
| ተከላ የተካሄድበት መሬት ስፋት | በሚ/ሄ/ር | 6.057 | 8 | 1 | 0.7718 | 77.2 | 0.8 | 0.716 | 89.5 | 0.6 | 0.6 | 0.748 | 100 | 2.4 | 2.944 | 100 |
| ያገገመ የተራቆተ የደን መሬት | በሚ/ሄ/ር | 3.9684 | 11 | 0.95 | 0.694 | 73.1 | 1 | 0.692 | 69.2 | 1 | 0.25 | 0.591 | 100 | 2.2 | 1.977 | 89.86 |
| የቀርከሀ ደን ማልማት | በሚ//ሄ/ር | | 0.2 | 0.02 | 0.0147 | 73.5 | 0.02 | 0.0675 | ›100 | 0.02 | 0.02 | 0.077 | 100 | 0.06 | 0.16 | 100 |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃ ፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንው ን | አፈፃፀ ም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲጎለብት የተደረገበት የመሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 1 | | | | | | | 0.1 | | 0.05 87 | | | 0.0587 | |
| ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ ማካሄድ | በመቶኛ | | 100 | | | | 50 | 15 | 30 | 100 | 10 | 10 | 100 | 60 | 25 | 41.67 |
| የደን ሽፋን መረጃ | በቁጥር | 1 | 5 | 1 | 1 | 100 | | | | | | | | 1 | 1 | 100 |
| የተዘጋጀ የደን ማኔጅመንት ፕላን | በሚ/ሄ/ር | 1.164 | 2 | 0.2 | 0.195 | 97.41 | 0.2 | 0.97 | 96.8 7 | 0.2 | | | | 0.4 | 1.165 | 100 |
| የደን አያያዝ የተሻሻለላቸው የከተሞች ብዛት | በቁጥር | 18 | 50 | 11 | 9 | 81.82 | 5 | 5 | 100 | 5 | 3 | 4 | 100 | 19 | 18 | 94.74 |
| ግብ 7. የደን ሀብት ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የደን ዘርፍ ለሀገራዊ ምርት የሚያበረከክተውን ድርሻ | በመቶኛ | 4 | 8 | | | | | | | | | | | | | |
| ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 2 | 4.62 | 2 | 2 | 100 | 2.12 | 2.283 | ›100 | 2 | 2.16 | 2.28 | 100 | 1.28 | 2.28 | 100 |
| አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 3.03 | 0.2 | 0.202 | 100 | 0 | | | 0.2 | | 0.05 25 | | 0.2 | 0.2545 | 100 |
| ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰል መጠን | ሚሊ/ቶን | 0 | 2 | 0.2 | 0.2014 | 100 | 0.2 | 0.345 | 100 | 0.2 | 0.06 7 | 0.15 2 | 100 | 0.467 | 0.6984 | 100 |
| ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን | ቶን (ሚሊዮን) | 0.1622 5 | 10.2 | 1.02 | 1.964 | 100 | 1.02 | 2.134 | 100 | 1.02 | 0.34 | 0.94 | 100 | 2.38 | 5.038 | 100 |
| በደን ዘርፍ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ብዛት | በሚሊዮን ቁጥር | 1.3 | 2.5 | 0.5 | 0.349 | 70 | 0.25 | 0.255 | 100 | 0.25 | 0.12 | 0.19 6 | 100 | 0.87 | 0.8 | 92.0 |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃ ፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንው ን | አፈፃፀ ም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሥርዓተ ምህዳሮች የሚያመነጩትን አገልግሎት ዋጋ ትመና የሚያሳይ መረጃ፣ | በቁጥር | | 4 | 3 | 3 | 100 | 1 | 1 | 100 | 1 | | | | 4 | 4 | 100 |
| ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን | በቢሊዮን ብር | 0.636 | 2.8 | 0.2 | 0.258 | 100 | 0.2 | 0.293 | 100 | 0.25 | 0.11 | 0.11 47 | 100 | 0.51 | 0.6657 | 100 |
| ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን | በሚሊዮን ዶላር | 6 | 278 | 20 | 12 | 60.15 | 20 | 2.442 | 12.2 | 26 | 7 | 7.68 2 | 100 | 47 | 22.124 | 47.1 |
| ግብ 8. የደን መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች | | 237 | 429 | 63 | 62 | 98.4 | 50 | 37 | 74 | 43 | 7 | 6 | 85.7 | 120 | 105 | 87.5 |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | 163 | 12 | 8 | 66.7 | 22 | 13 | 59 | 15 | | | | 34 | 21 | 61.8 |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | 98 | 30 | 36 | 100 | 9 | 9 | 100 | 13 | 4 | 2 | 50 | 43 | 47 | 100 |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | 110 | 16 | 13 | 81.3 | 13 | 10 | 77 | 9 | 3 | 4 | 100 | 32 | 27 | 84.4 |
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | 58 | 5 | 5 | 100 | 6 | 5 | 83.3 | 6 | | | | 11 | 10 | 90.9 |
| ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የተዘጋጁ የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ብዛት | | | 328 | 34 | 34 | 100 | | | | 41 | | | | 34 | 34 | 100 |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | | | | | | | | 13 | | | | | | |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | | | | | | | | 13 | | | | | | |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | | | | | | | | 8 | | | | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | | | | | | | | 7 | | | | | | |
| በታወቁ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ውጤቶች | በቁጥር | | 170 | | | | | | | 22 | | 7 | | | 7 | |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | | | | | | | | 9 | | 4 | | | 4 | |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | | | | | | | | 7 | | 1 | | | 1 | |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | | | | | | | | 3 | | | | | | |
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | | | | | | | | 3 | | 2 | | | 2 | |
| ለተጠቃሚዎች በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት የተሰጠ ስልጠና | በተሳታፊ ቁጥር | | 670 | 260 | 295 | 100 | 210 | 171 | 81.4 | 200 | | | | 470 | 466 | 99.1 |
| በተለያዩ የሚዲያ ቻናሎች እተደራሽ የተደረገ መረጃ ብዛት | በቁጥር | | 96 | 24 | 24 | 100 | | | | 12 | | | | 24 | 24 | 100 |
| ግብ 10 የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶች ድርሻ | በሚሊዮን ቁጥር | | 1.25 | 0.125 | 0.102 | 81.9 | 0.125 | 0.0723 | 57.8 | 0.063 | 0.0225 | 0.061 | 100 | 0.2725 | 0.2353 | 86.3 |
| የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች ድርሻ | በሚሊዮን ቁጥር | | | 0.125 | 0.197 | 100 | 0.125 | 0.12 | 96 | 0.125 | 0.15 | 0.1497 | 99.8 | 0.4 | 0.4667 | 100 |
| የተዘጋጀ የህፃናት ማቆያ | በቁጥር | | 8 | | | | | | | 2 | | | | | | |
| የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የተሰጠ ሥልጠናዎች ብዛት | በቁጥር | | 16 | | | | | | | 2 | 1 | | | | | |
| ግብ 11 ፡- የመሠረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃ ፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል G+5 ላቦራቶሪ ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | | 100 | | | | 30 | 15 | 50 | 100 | 40 | 23.6 | 59 | 40 | 23.6 | 59 |
| የደን ዉጤቶች እኖቬሽን ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | | 100 | 45.6 8 | 16.96 | 37.1 | 100 | 40 | 40 | 100 | 60 | 44.1 9 | 73.6 | 60 | 45.13 | 75 |
| አውቶሜት የተደረጉ የተቋሙን አሰራሮች | በቁጥር | | 2 | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች | በሄ/ር | | 371 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 100 |
| አዲስ የተቋቋሙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በቁጥር | | 5 | | | | | | | 2 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 |
| በመካሄድ ላይ የሚገኙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በሄ/ር | | 8 | | | | | | | 8 | 8 | 8 | 100 | 8 | 8 | 100 |
| ግብ 12 ፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የአጭር ግዜ ስልጠና ያገኙ ተመራማሪዎች | በቁጥር | - | | 53 | 53 | 100 | 76 | 76 | 100 | 164 | 164 | 86 | 51 | 293 | 215 | 73.4 |
| የረጅም ግዜ ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች | | | | | | | 46 | | | 73 | 73 | 73 | 100 | 73 | 73 | 100 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | 36 | | | 48 | 48 | 48 | 100 | 48 | 48 | 100 |
| በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | 10 | | | 24 | 24 | 24 | 100 | 24 | 24 | 100 |
| Post Doc | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው የረጅም ግዜ | | | | 40 | 65 | 100 | 52 | | | 73 | 73 | 73 | 100 | 73 | 73 | 100 |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስልጠና ላይ ያሉ ሠራተኞች ብዛት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 1 | | 1 | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 46 | | 26 | | | 48 | 48 | 48 | 100 | 48 | 48 | 100 |
| በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 17 | | 24 | | | 24 | 24 | 24 | 100 | 24 | 24 | 100 |
| Post Doc | በቁጥር | | | | 1 | | 1 | | | | | | | | | |
| ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት | ቁጥር | | 60 | | | | | | | 60 | 60 | - | 0 | | | |
| የተካሄደ የልምድ ልውውጥ ብዛት | በቁጥር | | 16 | 2 | 2 | 100 | | | | 2 | 2 | 2 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| **አማካይ** | | | | | | | | | | | | | | | | **93.34** |